Addis Express Media, 25.02.20



ልብ የሚነካው የዶክተር ደሳለኝ የህይወት መስዋዕትነት፤

(ከቅርብ ጓደኛ አንደበት)

"ዘርሽ እኔ ህዝብ እንዳያውቅ ስል ነው ጭንቀቴን የምደብቀው! .....! "ነበር ፤ ያለኝ ከቀናት በፊት ለደቂቃዎች በስልክ ስንጨዋወት፡፡ እኔ ግን አንተ ባትፈልግና ፈቃድህን ባልጠይቅ እንኳ ፥ ይኸን ለህዝብህ የከፈልከውንና እየከፈልከው ያለኸውን ትልቅ ዋጋ ላለማንሳት አልቻልኩም፡፡

ዶ/ር ደሳለኝ የአማራው ህዝብ የዘመናት ጥያቄ ፥ እውን የሆነበትን አብን እውን አርጎ የታላቁን ህዝብ አደራ ከተረከበበት ጊዜ አንስቶ እጅግ ተነግረው የማያልቁ ውጣውረዶችን አሳልፎ ዛሬ ላይ እንደደረሠ ነጋሪ ሳያሻ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገርግን ይኸኛው ትንሽ ከበድ ይላል፡፡

ለረዥም ጊዜ በህመም የሚሠቃዩ ወላጅ እናቱን ፥ ሆስፒታል አስተኝቶ ለህዝቡ ትግል በሁሉም ቦታ የመገኘትን ዋጋ የሚረዳው ፥ በሞት አፋፍ ላይ ሁና ያለችን እናት የመመልከትን ጭንቀትና ህመም የሚረዳ ሠው ብቻ ነው፡፡ ዶክተር ግን ለአንዳችን እንኳ ይኸን ጭንቀቱን ሳያጋራ ፥ ሳምንት እንቅልፍ አጥቶ ሆስፒታል እያደረ እናቱን አስታሞ ፥ ተመልሶ ደግሞ በትግል ጉዳዮች ላይ በሁሉም ቦታ ይገኛል፡፡ ይህ ሲሆን ግን ለጓዶቹ ከፈገግታ ውጭ አንዳችም የጭንቀት ምልክት አያሳየንም ነበር፡፡ ታዲያ እንዲህ እያደረገ ረዥም ጊዜያት ቢቆጠሩም ፥ ለአንድም ሠው ቃል መተንፈስን ከቶውንም አይፈልግም፡፡ ወላጅ እናቱም ዛሬም በሆስፒታል አልጋ ላይ ናቸው፡፡

ታዲያ! ዛሬ አንድ የዶ/ርን እናት ለመጠየቅ ወደሆስፒታል ሂዶ የነበረ ሠው ያጫወተኝ እውነት በእጅጉ ልቤን አደማው! ስለእውነት በፅናቱ በእጅጉ ተደመምኩ፡፡ ይህ ሠው ወደሆስፒታል ሲያመራ ፤ የእናቱ ጤንነት ከጊዜ ወደጊዜ አለመሻሻሉ ጭንቀት ውስጥ የከተተው መሪአችን ዶ/ር ደሳለኝ ፥ አይኖቹ በእንባ ተሸፍነው :- << ከሁለት አመት በፊት ሆኖ ቢሆን ፥ ስራ በደንብ እሰራ ስለነበር ፥ እናቴን አንዱ ሀገር ወስጄ የማሳከም አቅም አላጣም ነበር! አሁንማ ምን ማረግ እችላለሁ? .... >> ነበር ፤ ሲል የመለሠለት፡፡ ይህ በእውነት ልብ ያደማል፡፡ ስለህዝቡ የከፈለውን እጅግ ትልቅ ዋጋ ከዚህ ብቻ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ በውስጣችን ልናስቀምጠው የሚገባ በሚዛን የማይደፈር የተከፈለልን ዋጋ ነው!!! ይህ እኛነታችን የሚፈተንበት ስለእኛ የተሆነልን መከፈል ነው!!!

እግዚአብሄር ለዶር ደሳለኝ ብርታቱን ይስጠው። እናቱንም ይፈዉሳቸው።"

ዘሪሁን